<u>በየካ ክፍለ ከተማ በወረዳ ፰ የ ፳፱፻፯ ዓ.ም ለ፰ኛ ክፍል የተዘጋጀ የሞዴል ፈተና</u>

መመሪያ አንድ፦ ከተራ ቁጥር ፩ እስከ ፲ ያሉትን ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበ ምንባብ ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ምንባቡን በጥሞና በማንበብ ለጥያቄዎቹ
እንደአጠያየቃቸው ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

ምንባብ

የማለዳ ቁርስ ለመቋደስ ወደተለመደው የምግብ ጠረጴዛ እንደደረሰ ቆማ የተቀበለችውን የልጇን ገጽታ ልብ ብሎ አስተዋለ። ኩርፊያና ቅሬታ አላየበትም። ስለጓደኛዋ ችግርና ስላሰበችው እርዳታ ጉዳይ በተመለከተ የተናገራትን ተግሳጹንና ምክሩን ሙሉ በሙሉ እንደተቀበለችው አሰበ።ማህሌተ ጽጌም ፈገግታዋን ከሰላምታ ጋር ከማቅረብ ውጪ በወሰነችው መሰረት አባትዋን ዳግመኛ ስለጓደኛዋ አላነሳችበትም።

ከቁርስ በኋላ አቶ ዘመንፈስ መኪናውን ለማቆም ወደውጭ ሲወጣ ማህሌተ ጽጌ ደግሞ የደብተሮችዋን ቦርሳና የምሳ እቃዋን ለመውሰድ ወደ ዲና ሄደች።እንደተለመደው የሷ የምሳ እቃና ሌላም ምሳ መያዣ በቦርሳዋ ውስጥ ተከቶ አገኘችው።የደብተርዋ ቦርሳ ደግሞ ከምን ጊዜውም በዚያን ቀን አበጥ ብሎ ተወጥሮ ታየ።ምክንያቱ ደግሞ በተነጋገሩት መሰረት ሌላኛው የምሳ እቃና እንዲሁም የማትጠቀምባቸው ጥቂት የማህሌተ ጽጌ ልብሶች ተጨምረውበት ስለነበር ነው።የአባትዋን መኪና ጡሩንባ እንደሰማች ሁለቱም በሞቀ ፈገግታ ተያዩ።ማህሌተ ጽጌም ቦርሳዋን አዝላ፣ ዲናን ሳመቻትና ፈጥና ወደመኪናው ሄደች።

ለአመታት በተለመደው ስርዓት መሠረት አቶ ዘመንፈስ እያንዳንዱን የስራ ቀን ይጀምር የነበረው ብቸኛ ልጁን ማህሌተ ጽጌን ትምህርት ቤት በማድረስ ነው። በዚያን ቀንም ከ “እቴጌ ጣይቱ ብርሃን ዘኢትዮድያ “ ትምህርት ቤት የግቢ አጥር መግቢያ አጠገብ ልጁን አውርዷትና ተሰናብቷት ሄደ።

በተማሪዎች ተጠልላ የአባትዋን ርቆ መሄድ ካየች በኋላ ማህሌተ ጽጌ በየአቅጣጫው ሳባን በአይኖችዋ ፈለገቻት። ከእነማህሌተ ጽጌ በፊት ከወንድሟ ጋር የደረሰችው ሳባ ከመንገድ ማዶ ቆማ ስለነበር የወንድሟን እጅ ይዛ መንገዱን ስታቋርጥ አየቻትና ደስ አላት።ከዋናው መግቢያ በር በስተቀኝ ጠርዝ ላይ ተገናኝተው ሳባና ማህሌተ ጽጌ ሰላምታ ተለዋውጠው ተሳሳሙ።ሳባም ከተል አድርጋ “ታናሽ ወንድሜ ናሆም ይሄኼ ነው ፤ተዋወቁ .....“አለችና የአስራ ሁለት አመቱን ናሆምን ወደ ማህሌተ ጽጌ ቀረብ አደረገችው።

“ሀይ ናሆም .....እንደምን አለህ? እኔ ማህሌተ ጽጌ እባላለሁ። የሳባ ጓደኛ ነኝ ። ያንተም ጓደኛ እሆናለሁ። አለችው ከጨበጠችው በኋላ ሳብ አድርጋ በማቅረብ እየሳመችው በአጸፋው ቢስማትም ናሆም ምንም ሳይናገር አንገቱን ደፍቶ ቆመ። ማህሌተ ጽጌም የሳባን ሁለንተና በሀዘኔታ ቃኘችው።

“ሳባዬ ....ሁልጊዜ በዚህ ሰዓት አባቴ ከሄደ በኋላ እዚህ ቦታ ቆሜ እጠብቅሻለሁ። የምሳ እቃሽን ካቀበልኩሽ በኋላ ከአካባቢው ቶሎ ትሄጃለሽ።ለማንም ስለምናደርገው ግንኙነት አንቺም ናሆምም እንዳትናገሩ።“ አለችና ቦርሳዋን ከፍታ በመጀመሪያ ያመጣችላትን ልብስ ሰጠቻት። ቀጥላም ሙቀቱ ያልበረደውን የምግብ እቃ አቀበለቻት። በዚህ ጊዜ የናሆም አይኖች ከዕቃው ላይ ተሰክተው ቀሩ።ደጋግሞ ምራቁን ዋጠ።

በዚህ ጊዜ ማህሌተ ጽጌ እንደዘበት የናሆምን ሁኔታ ልብ ብላ አየችው። ያልተጫሙት እግሮቹ በቀጭና በጭቅቅት ቆዳቸው ተሰንጣጥቆ ተጎድቷል።ልብሱም ከመቆሸሹ ሌላ የተቀደደ ነበር። ሌላ ሀዘን ልቧን ወጋው።

ምንጭ ከተባ ትሩፋት በደራሲ ፀሀይ መላኩ በ፳፻፲፬ ዓ.ም ከተዳፈው መጽሀፍ የተወሰደ።

፩. ለመቋደስ ሲል ምን ለማለት ፈልጎ ነው?

ሀ. ለመባረክ ለ. ለመመጽወት ሐ.ለመመገብ መ. ለመቀደስ

፪.“ዳግመኛ ስለጓደኛዋ አላነሳችበትም ።“የተባለው ጉዳይ ምንድነ?

ሀ. ተግሳጽና ምክሩን ለ. ኩርፊያና ቅሬታውን

ሐ. ተግሳጽና ምክርን ስለመቀበሏ መ.የጓደኛዋን ችግርና ያሰበችውን እርዳታ

፫. ለአመታት በተለመደው ሥርዓት መሠረት የሚለው ምኑን ለመግለጽ ተፈልጎ ነው?

ሀ. የልጁን ብቸኝነት ለማመልከት ለ. የአቶ ዘመንፈስን የስራ ውሎን ዘርዝሮ ለማመልከት

ሐ. የማህሌት ጽጌን ስራ መ. አቶ ዘመንፈስ በማለዳ የሚከውነውን ተግባር ለማሳየት

፬.ይህ ጽሁፍ በስንት አንቀጽ የተከፋፈለ ነው?

ሀ.በስድስት ለ. በአራት ሐ. በሰባት መ. በአምስት

፭. ትረካው የተጻፈው /የተተረከው / በስንተኛ መደብ ነው?

ሀ. በአንደኛ መደብ ለ. በሶስተኛ መደብ ሐ. በሁለተኛ መደብ መ. ሁሉም መልስ ናቸው።

፮.የማህሌተ ጽጌ ልብ በሀዘን የተወጋው ለምንድነው?

ሀ.የናሆም አይኖች ከምሳ እቃው ላይ ስለቀረ ለ. አካሉ የተጎሳቆለ በመሆኑ

ሐ. የጓደኛዋ ወንድም ስለሆነ ሐ. ወንድ በመሆኑ

፯. “ያልተጫሙት“ የሚለው ቃል በምንባብ ውስጥ ያለው አውዳዊ ፍቺ_____ነው።

ሀ. ያላደረገው ለ. ያላጠለቀው ሐ. ያደረገው መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው።

፰.ተጠልላ ለሚለው ቃል ተቃራኒ ሊሆን የሚችለው

ሀ. ፊለፊት ሆና ለ.ተሸፍና ሐ. ተከልላ መ. ተደብቃ

፱. "ደጋግሞ ምራቁን ዋጠ።" ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሀ. አማረው ለ. ከጀለ ሐ.ተመኘ መ.ሁሉም

፲. ይህ ድርሰት በስንት ዓ.ም ተጻፈ?

ሀ. በ 2014 ዓ.ም ለ. በ 2015 ዓ.ም ሐ. በ 2004 ዓ.ም መ. በ 1994 ዓ.ም

<u>መመሪያ ሁለት፦ ከተራ ቁጥር ፲፩ አስከ ፴፩ የተለያየ ይዘት ያላቸው ጥያቄዎች ቀርበዋል። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የሚሆናቸውን ምረጥ/ምረጪ</u>

፲፩. ከሚከተሉት ቃላት መካከል ውስጠ ግንድ ቅጥያን የያዘ የቱ ነው?

ሀ. ስራስር ለ አበቦች ሐ ተማሪዎቻችን መ. ሁሉም መልስ ናቸው

፲፪. በወደረኛ መስተዋምር የተገለጸው አረፍተ ነገር

ሀ. አባትህን ወይም እናትህን ማምጣት አለብህ።

ለ. ስለአባትህ ስራ ጠየኩህ እንጂ ስለእናትህ አልጠየኩህም።

ሐ. አባትህን እና እናትህን በስራ ማገዝ አለብህ።

መ. ሀ እና ሐ መልስ ናቸው።

፲፫. ከሚከተሉት መካከል ለቃላዊ ግጥም ባህሪ ትክክል የሆነው

ሀ. ተለዋዋጭነት ያለው መሆኑ። ለ. በመነበብ የሚከወን መሆኑ።

ሐ. ተናጠላዊ ክዋኔ መለያው ስለሆነ መ. ፅሁፋዊ መሆኑ

፲፬. የውስጥን ስሜት አውጥቶን በመናገር መፍትሔ ሊገኝ እንደሚቻል የሚያመላክት ምሳሌያዊ አነጋገር የትኛው ነው?

ሀ. ያልጠረጠረ ተመነጠረ ለ. በሽታውን የደበቀ መድኃኒት የለውም

ሐ. አልሞት ባይተጋዳይ መ. የሚወዱትን እቅፍ የጠሉትን ንቅፍ

፲፭. ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሀሳቦችን እያመዛዘኑ የሚጻፍበት የድርሰት ዓይነት_____ይባላል።

ሀ. አከራካሪ ለ.ገላጭ ሐ. ተርሰኪ መ. ስእላዊ

፲፮. ስለአንቀፅ ትክክል የሆነው አገላለፅ የቱ ነው?

ሀ. በውስጡ የተለያዩ ዝርዝር ሀሳቦችን አካቶ ይይዛል።

ለ. የአንቀፁን ዋና ሀሳብ የሚያብራሩ ሃሳቦችን ይይዛል።

ሐ. በአንቀፅ ውስጥ አንቀፁን የሚገልፅ አንድ ዋና ሀሳብ ይኖረዋል።

መ. ሁሉም መልሶች ናቸው።

፲፯. በመንስኤና ውጤት ግንኙነት ላይ የተመሠረተው የትኛው አረፍተ ነገር ነው?

ሀ.የት/ቤቱ ተማሪዎች ያለ እድሜያቸው የፍቅር ግንኙነት ጀመሩ።

ለ. በአብዛኞቹ ሴት ተማሪዎች ያለ እድሜያቸው የሰራ ጫና ተሸክመው ይታያሉ።

ሐ. ያለ እድሜያቸው የፍቅር ግንኙነት እያደረጉ ራሳቸውን ለችግር አጋለጡ።

መ. ሁሉም መልስ ናቸው።

፲፰. ለጠላ ይጠመቃል ከተባለ ለጠጅ _____ ይባላል?

ሀ. ይፈላል ለ. ይደፈደፋል ሐ. ይጣላል መ.ይዘፈዘፋል

፲፱. የራስን የህይወት ታሪክንና የግለሰብ የህይወት ታሪክን ለመዳፍ የጋራ መመሪያ የማይሆነው የትኛው ነው?

ሀ. የአስተዳደግ ሁኔታን መግለፅ ለ. የትምህርት ደረጃን መግለፅ

ሐ. የተበረከቱ አስተዋፅኦዎችን መግለፅ መ. የሞት ዘመንን መግለፅ

፳. ሰለገንዘቦቻቸው ለሚለው ቃል የምዕላድ አከፋፈሉ ትክክል የሆነው አማራጭ የቱ ነው?

ሀ. ስለ___ገንዘብ___ኦች ___አቸው ለ. ሰ___ለ___ ገንዘብ___ቻ___አቸ___ው

ሐ. ሰለ___ገንዘብ___ኦች___ ቸው መ. ስለ___ገንዘብ___አቸው

፳፩. ከሚከተሉት መካከል የቅኔ አፈታት ዘይን የሚገልጽልንን ትክክለኛ ሀሳብ ያልያዘው የትኛው ነው።

ሀ.ታሪክን ጠንቅቆ ባለማወቅ ለ. ቃላትን ከቃላት ጋር በማጣመር

ሐ. ቃላትን በማጥበቅና በማላላት መ. ከቃል ውስጥ ምዕላድን ፈልቅቆ በማውጣት

፳፪. የዘጠነኛ ክፍል ትምህርቴን በመማር ላይ እገኛለሁ። ይህ አረፍተ ነገር የተገለፀበት ጊዜ _____ ጊዜ ነው።

ሀ. የቅርብ ኃላፊ ለ. የአሁን ሐ. የትንቢት መ. ጊዜው አይታወቅም

፳፫. አዕሮተ ቃላትን ለመመስረት የምንጠቀምበት ስርአተ ነጥብ ምን በመባል ይታወቃል?

ሀ. ነቁጥ ለ. ትእምርተ አጋኖ ሐ. ሕዝባር መ. ከ "ሀ" እና "ሐ" መልስ ናቸው።

፳፬. የእነገስጥ ወላጆች <u>ከጎጃም</u> መጡ። የተሰመረበት ቃል አገባቡ ምንን ያመለክታል?

ሀ. ስም ለ. ግስን ሐ. ቅፅልን መ. ተውሳከ ግስን

፳፭. ቡልኮ ለሚለው ቃል ተመሳሳይ ፍቺሊሆን የሚችለው የትኛው ነው?

ሀ. ሙሉ ልብስ ለ.ጋቢ ሐ. ነጠላ መ.የለሊት ልብስ

፳፮. የሰው ልጅ ከተፈጥሮ ጋር ያለው <u>መስተጋብር</u> ውስብስብ ነው። ለተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺ የሚሆነው

ሀ. ውጊያ ለ. ክፍፍል ሐ. መተጋገዝ መ. ግንኙነት

፳፯.የቢጋር ጥቅም ሊሆን የሚችለው የትኛው ነው?

ሀ. ድርሰቱ ከተፃፈ በኋላ የሀሳቡን መቀናጀትና መጣጣም ለማየትና ለማስተካከል።

ለ. ጽሁፉ ሲያበቃ ከዋናው ሀሳብ እንዳያፈነግጥ ይረዳል።

ሐ. መልእክትን ለመቀበል ራሱን የቻለ መሣሪያ አለመሆኑ።

መ. የድርሰቱን አላማ ግልጽ ለማድረግና ድርሰቱን ከአላማው ጋር ለማስማማት ያግዛል።

፳፰. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ ስም የሆኑ ቃላትን ተቆጣሪ መሆናቸውን የሚጠቁመን ጥገኛ ምእላድ የትኛው ነው?

ሀ. _ኦች ለ. _ኣት ሐ. እነ_ መ. ሁሉም መልሶች ናቸው።

፳፱.ለሰራችሁት የቤት ስራ እርማት ውሰዱ! ይህ ዓረፍተ ነገር ከየትኛው አይነት ይመደባል?

ሀ.ትእዛዛዊዓረፍተ ነገር ለ.መጠይቃዊ ዓረፍተ ነገር

ሐ.አሉታዊ ዓረፍተ ነገር መ.ሁሉም መልስ ናቸው ።

፴.የአሁን ጊዜ ግስ ሊያስቀድም የሚችለው ምእላድ የቱ ነው?

ሀ.“እየ_የሚለውን ምእላድና "ነው“ የሚለው ረዳት ግስ ለ. ምንም የተለየ ምእላድ የለውም።

ሐ. “እየ_ የሚለውን ምእላድና "ነበር“ የሚለው ረዳት ግስ መ.ሀ እና ሐ መልስ ናቸው።

፴፩. ከሚከተሉት ዝርዝር ቃላት ውስጥ በፊደል ገበታ አቀማመጥ የተቀመጠው የቱ ነው?

ሀ. እወጃ ፣ የእናት ፣ ቁማር ፣ ጭምት ፣ ትፍትፍ ፣ ጢባጢቤ

ለ. ትፍትፍ ፣ ቁማር ፣ ጢባጢቤ ፣ ጭምት ፣ የእናት ፣ እወጃ

ሐ. ቁማር ፣ ትፍትፍ ፣ እወጃ ፣ የእናት ፣ ጢባጢቤ ፣ ጭምት

መ. ቁማር ፣ እወጃ ፣ ትፍትፍ ፣ የእናት ፣ ጢባጢቤ ፣ ጭምት

፴፪. ከሚከተሉት መካከል የቋንቋ መዋቅርን ቅደም ተከተል ጠብቆ የተቀመጠው የቱ ነው?

ሀ. ቃል ፣ ድምጽ ፣ ሀረግ፣ ዓረፍተ ነገር፣ አንቀጽ፣ ድርሰት

ለ. ፊደል ፣ ድምጽ፣ ሀረግ፣ ቃል፣ ዓረፍተ ነገር፣ አንቀጽ፣ ድርሰት

ሐ. ድምጽ፣ ቃል፣ ሀረግ፣ ዓረፍተ ነገር፣ አንቀጽ፣ ድርሰት

መ. ድምጽ፣ ፊደል፣ ዓ.ነገር፣ ሀረግ፣ አንቀጽ፣ ድርሰት

፴፫.በአንቀፅ ውስጥ ዋናውን ሀሳብ ጨምቆ የሚይዝ

ሀ. ኃይለ ቃል ለ.መዘርዝር ሐ. ዓረፍተ ነገር መ. አንቀፅ

፴፬. ልጁ የያዘው ሸንኮራ <u>ለጋ</u> ነው። ሀዳኑ ልጅ ኳሱን <u>ለጋ</u>። የተሰመረባቸው ቃላት ትክክለኛ አነባበብ የሚሆነው የቱ ነው?

ሀ. በመጀመሪያው አረፍተ ነገር ጠብቆ ፣በሁለተኛው ላልቶ ለ. በሁለቱም ላልቶ

ሐ. በመጀመሪያው ዓረፍተ ነገር ላልቶ፣ በሁለተኛው ጠብቆ መ. በሁለቱም ጠብቆ

መመሪያ ሶስት፦ ከተራ ቁጥር ፴፭ እስከ ፴፰ ድረስ ለተዘረዘሩት ቃላት ተቃራኒ ፍቺ የሚሆኖቸውን ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የሚሆኖቸውን ፊደል ምረጥ/ምረጪ

፴፭. በከለ ሀ.አሳደፈ ለ. አቆሸሸ ሐ.አስተላለፈ መ. አነጣ

፴፮. ደመቀ ሀ. ተዋበ ለ.ፈዘዘ ሐ. አማረ መ.ደራ

፴፯.ስንጥር ሀ.ግንዲላ ለ. ስንተጋ ሐ. ስንጥቅጣቂ መ. የእንጨት ስንጣቂ

፴፰.ጭፍቅ ሀ. ጥቅጥቅ ያለ ለ. ችፍግ ያለ ሐ.ዘርዘር ያለ መ.ጥሻ

መመሪያ አራት፦ ከተራ ቁጥር ፴፱ እስከ ፵፭ ድረስ ለተዘረዘሩት ቃላት ፍካሬያዊ ፍቺ የሚሆኖቸውን ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የሚሆኖቸውን ፊደል ምረጥ/ምረጪ

፴፱. መሬት

ሀ. ምድር ለ. የእርሻ ቦታ ሐ. ዝምተኛ መ. የብስ

፵. ተልባ

ሀ. የቅባት እህል ለ. የሚበላ ሐ. አቋም የሌለው መ. ጀግና

፵፩. ጎጆ

ሀ. መኖሪያ ቤት ለ. ከሳር የተሰራ ቤት ሐ. መጠለያ መ. ትዳር

፵፪. አተላ

ሀ. የማይረባ ለ. የጠላ ዝቃጭ ሐ. ተረፈ ምርት መ. አበላሽ

፵፫. አሽከር

ሀ. ልጅ ለ. አገልጋይ ሐ. ተቀጣሪ መ. ተከታይ

፵፬. አሳማ

ሀ. ሆዳም ለ. ወፍራም አጭር እንስሳ ሐ. ሀሜትን ፈቀደ መ.በክፉ አነሳ

መመሪያ አምስት፦ ከተራ ቁጥር ፵፮ እስከ ፶ ድረስ ለተዘረዘሩት ቃላት ጠብቀው ሲነቡ የሚሰጡትን ፍቺ ከተሰጡት አማራጮች

መካከል ትክክለኛ መልስ የሚሆናቸውን ምረጥ/ምረጪ.

፴፭. ይገባል ሀ. ይዘልቃል ለ. ይረዳል ሐ. ያስፈልጋል መ. ይሆናል

፴፮. በላት ሀ. ንገራት ለ. ተመገባት ሐ. ምታት መ. አውራት

፴፯. ቀላ ሀ. ቆረጠ ለ. አረደ ሐ. ቀይ ሆነ መ. ሁሉም

፴፰. ይረዳል ሀ. ያገለግላል ለ. ያግዛል ሐ. ይጠቅማል መ. ይገነዘባል

፴፱. አባይ ሀ. የወንዝ ስም ለ. ዋሾ ሐ. ቀላማጅ መ. ባለበት የማይገኝ

፵. ጠብ ሀ. አለመስማማት ለ. ወደቀ ሐ. እልፍ መ. ጥል

መመሪያ ስድስት፦ ከተራ ቁጥር ፵፩ እስከ ፵፭ ድረስ ለተዘረዘሩት ምሳሌያዊ አነጋገሮች በመልእክት የሚስማማቸውን ከተሰጡት አማራጮች መካከል መልስ የሚሆናቸውን ምረጥ/ምረጪ.

፵፩. ሲጎርሱ በልክ ሲታጠቁ ጠበቅ

ሀ.በአቅምና በመጠን መኖር እንዳለብን

ለ.ኑሮን በአግባቡ ካልተኖረ ችግር እንደሚከሰት

ሐ. ማንኛውንም ነገር ከመጠን በላይ ከተጠቀምን አደጋ እንዳለው

መ. ሁሉም መልስ ናቸው።

፵፪. ያደፈውን በእንዶድ የጎደለውን በሞረድ

ሀ. ያልተስተካከለን ነገር ማስተካከል እንደሚገባ ለማሳየት

ለ. የተበላሸን ነገር ዝም ብሎ መተው እንዳለበት ለማሳየት

ሐ. ቢበላሽም ቢጠፋም ችግር እንደሌለው ለማሳየት

መ. የጎደለ ነገር መሟላት እንደማይችል ለማሳየት

፵፫. ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባል

ሀ. ባለቤት ያሳየውን ነገር ሌላም ተከትሎ እንደሚፈጽም

ለ. ስም ከቤት ይጣል ጎረቤትም በዛው ይከተላል

ሐ. ባለጉዳዩ ያላከበረውን ነገር ሌላውም እንደማያከብረው

መ. ሁሉም መልስ ናቸው።

፵፬. የሰው ወርቅ አያደምቅ

ሀ. የራስ ያልሆነ ነገር ጥሩ እንደሆነ

ለ. በሰው ስራ መመሰገን እንደማይቻል

ሐ. የሰውን ወርቅ ሲያደርጉት ውበት እንደሌለው

መ. የራስ ባልሆነ የወርቅ ጌጥ ማጌጥ ደስ ስለማይል

፵፭. አመድ በዱቄት ይስቃል

ሀ. አመድ የተባለው ነገር ዱቄት ላይ ሲሰቅ ታየ

ለ. የራስን ችግር ሳያውቁ ስለሌላው እንከን ማውጣትየራሱን

ሐ. የተሻለው ነገር ባልተሻለው ነገር ላይ ያፈዛል

መ. ችግር የሚያውቅ በሰው ችግር ይዘባበታል

መመሪያ ሰባት፦ ከተራ ቁጥር ፱፯ እስከ ፷ ድረስ ለተዘረዘሩት ቅኔዎች የወርቅ ፍቺያቸውን ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የሚሆናቸውን ምረጥ/ምረጪ

፱፯. አብረን ተቀምጠን መልካችን አንድ ነው
አሁን እኔና እሷን የሚለየን ማነው
ሀ. በመልክ አንድ አይነት ነን ለ. እኔን እና እሷን የሚለያየን የለም
ሐ. ስንታይ እህትና ወንድም እንመስላለን መ. አልተስማማንም ማን ይለየን

፱፯. እንጫወት ይላል ስራ ፈት ሰው
እኔ ባል ደርሶብኝ ተጨንቄያለው
ሀ. ባለቤቴ መጥቶብኛል ለ. ድግስ ደርሶብኝ ደፋቀና እያልኩ ነው
ሐ. በበአል ቀን ተጨንቄ ዋልኩኝ መ. ሁሉም ወርቅ መሆን ይችላሉ።

፱፰. ዘግቼ ቆልፌ የተውኩትን እልፍኝ
ከፍተሽ መቆየትሽ በጣም አሳዘነኝ
ሀ. በሩን ባለመዝጋትሽ አዘነኩኝ ለ. የተዘጋውን ቤት ስለከፈትሽው ተደስቻለሁ
ሐ. ክፉ በመሆንሽ አዘንኩብሽ መ. በሩን በርግደሽው ቆየሽ

፱፱. ሱሪዬን አንጥፌ ልተኛ ደጅሽ
ከቤት እንዳልገባ አንቺምነት የለሽ
ሀ. መኝታ የለሽም ለ. ታማኝ አይደለሽም
ሐ. ቤትሽ ቁልፍ የለውም መ. ለመኝታ የሚሆን ቁርበት የለሽም

፷. ለግርግዳው ነወይ የምትቸገሪ
ቀርጨልሻለሁ ከእንግዲህ ቤትስሪ
ሀ. ለግርግዳ የሚሆን ነገር አዘጋጅቼልሻለሁ ለ. ቀርጬ ላስኩት
ሐ. እንጨቱ ተዘጋጅቷል መ. ቤቱን ለመስራት አትቸገሪም

መልካም ፈተና

አዘጋጅ ብሩህ ተስፋ የቅ/መ/ እና የመ/ደ/ት/ቤት

መልስ

፭. ሐ	፸፭.ሀ	፺፭.መ
፪. መ	፸፪.ለ	፺፪.ሀ
፫. መ	፸፫.መ	፺፫.ሀ
፱. ሐ	፸፱.መ	፺፱.ሀ
፭. ለ	፸፭.ለ	፺፭.ሐ
፯. ለ	፸፯.መ	፺፯.ለ
፯. መ	፸፯.መ	፺፯.መ
፵. ሀ	፸፵.መ	፺፵.መ
፱. መ	፸፱.ሀ	፺፱.ሀ
፲. ሀ	፴.ሀ	፶.ለ
፲፭.ሀ	፴፭.ሐ	፶፭.መ
፲፪.መ	፴፪.ሐ	፶፪.ሀ
፲፫.ሀ	፴፫.ሀ	፶፫.መ
፲፱.ለ	፴፱.ሐ	፶፱.ለ
፲፭.ሀ	፴፭.መ	፶፭.ለ
፲፯.መ	፴፯.ለ	፶፯.ለ
፲፯.ሐ	፴፯.ሀ	፶፯.ሀ
፲፵.ሐ	፴፵.ሐ	፶፵.ሐ
፲፱.መ	፴፱.ሐ	፶፱.ለ
፭. ሀ	፺. ሐ	፵.ለ